መልእክት ሦስት

## በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ የአማኞች የጸጋ ልምምድ
## ሕይወታዊዋ የክርስቶስ አካል በሆነችው በቤተ ክርስቲያን መጠናቀቁ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ዮሐ. 1፡16፤ ሮሜ 12፡6፤ 1 ቆሮ. 1፡2-4፤ 2ቆሮ. 13፡14፤
ገላ. 6፡18፤ ኤፌ. 4፡7፣ 29፤ ፊል. 4፡23፤ ራእ. 22፡21

**I. በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ በጸጋ ሥር የሆነው የአዲስ ኪዳን አማኞች ኑሮ በሂደት ያለፈውን እና የተጠናቀቀውን ሦስታንዱን አምላክ እንደ ጸጋ የመለማመድ ጥቅል ኑሮ ነው—ገላ. 6፡18፤ ዕብ. 4፡16፤ ራእ. 22፡21፡-**

ሀ. የክርስቲያን ኑሮ የጸጋ ኑሮ፣ የጸጋ ልምምድ መሆን አለበት፤ የክርስቲያን ሕይወታችን መሠረታዊ በሆነ መልኩ እግዚአብሔር እንደ ጸጋችን የእኛ የሆነበት ሕይወት ነው—2 ቆሮ. 1፡12።

ለ. ጥቅል ኑሮ ማለት መላው ኑሯችን ለእኛ ጸጋ ለመሆን በሂደት ያለፈው የሦስታንዱ አምላክ ኑሮ ነው—13፡14።

ሐ. የተቀመመው መንፈስ በሂደት ያለፈውን ሦስታንዱን አምላክ እንደ ጸጋ እንደሰተው ዘንድ በየዕለቱ እንደ ቅባቱ በእኛ ውስጥ እየተንቀሳቀሰ ነው—1 ዮሐ. 2፡20፣ 27።

መ. የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የጸጋ መንፈስ የሦስታንዱ አምላክ ማደሪያና መያዣ ዕቃ ለመሆን ዳግም ከተወለደው ከመንፈሳችን ጋር ነው—ዕብ. 10፡29፤ ገላ. 6፡18፤ ፊልጵ. 4፡23፤ ፊልሞና 25፤ 2 ጢሞ. 4፡22።

ሠ. ጸጋን፣ ማለትም ሦስታንዱን አምላክ—አብ በወልድ የተሰጠንን፣ ወልድ በመንፈሳችን ባደረው መንፈስ እውን የሆነልንን—የተቀበልን ሰዎች ነን—1 ቆሮ. 15፡45፤ 6፡17።

ረ. እኛ ቅዱሳን ስለሆንን በእያንዳንዱ የየዕለት ሕይወታችን ገጽታ የጌታ ጸጋ ከእያንዳንዳችን ጋር መሆን አለበት—ፊልጵ. 4፡23፤ ኤፌ. 4፡7።

**II. እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን የምትመሠረተው በክርስቶስ ኢየሱስ በተሰጣት ጸጋ ነው—1 ቆሮ. 1፡2-4፡-**

ሀ. የእግዚአብሔር ጸጋ ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው በመንፈሳዊነቷ ላይ ወይም ቤተ ክርስቲያኒቱ ባላት ሁኔታ ላይ በመመሥረት አይደለም።

ለ. የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻውን የቤተ ክርስቲያን መሠረት ነው—16፡23።

ሐ. በ 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡4 ላይ ጳውሎስ እግዚአብሔርን ያመሰገነው ለቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ በተሰጠው በጸጋ ስጦታ ላይ ተመሥሮቶ ነበር።

መ. ቤተ ክርስቲያን ተጨማሪ ጸጋ ትቀበል ዘንድ በጸጋ መሠረት ላይ ቆማለች—ራእ. 22፡21።

ሠ. ጸጋን እንደመሠረታችን ተቀብለናል፣ የቆምነውም በጸጋ ላይ ነው እንጂ በብቃቶቻችን፣ በሰናይ ባሕሪዎቻችን ወይም በልቀቶቻችን ላይ አይደለም፤ ስለዚህ ተጨማሪ ጸጋ ለመቀበል፣ ብሎም በጸጋ ላይ ጸጋ ለመቀበል ብቁ ተደርገናል—ዮሐ. 1፡16።

**III. አማኞች በኢኮኖሚው የእግዚአብሔር ጸጋ ልምምዳቸው መጠናቀቅ ሕይወታዊ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ናት—1 ቆሮ. 12፡12-13፣ 27፤ ኤፌ. 1፡6-8፣ 22-23፡-**

ሀ. ጸጋ የሚዘዋወረው ሦስታንዱ አምላክ እርሱ የሆነውን ሁሉ ለድሰታችን ማደሉ ነው፤ መላው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት የመለኮታዊው ሥላሴ በውስጣችን መዘዋወር በሆነው በጸጋ ላይ ይመረኮዛል—1 ጴጥ. 5፡10፤ ሐዋ. 4፡33፤ 2 ቆሮ. 8፡1፤ 13፡14።

ለ. የክርስቶስ አካል ተግባራዊ ሕይወት እና ግንባታ ከእግዚአብሔር ጸጋ ውስጣዊ ድሰታ ይመጣሉ—1 ቆሮ. 1፡9፤ 2 ቆሮ. 13፡14።

ሐ. እያንዳንዱ የሕይወታዊው ክርስቶስ አካል ክፍል በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ የእግዚአብሔር ጸጋ ውጤት ነው—ሮሜ 12፡4-6።

መ. በአካሉ ውስጥ በተሰጠን ጸጋ መሠረት የተለያዩ ስጦታዎች እና የክርስቶስ ጸጋ ልምምዳችን ውጤት የሆኑ ስጦታዎች አሉን—ቁ. 6፡-

1. ይህ ጸጋ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሕይወታችን ይሆን ዘንድ ለድሰታችን እንደ መለኮታዊው ንጥረ-ነገር ወደ ማንነታችን ውስጥ መምጣቱ ነው—ዮሐ. 1፡16፤ 2 ቆሮ. 13፡14።

2. ይህ ጸጋ ወደ ውስጣችን ሲመጣ፣ እግዚአብሔርን ለማገልገል በክርስቶስ አካል ውስጥ እናገለግል ዘንድ የሕይወት እድገታችንን በማጀብ በሕይወት ወደሆኑ ስጦታዎች የሚዳብሩትን የተወሰኑ የመንፈሳዊ ክሕሎቶችንና ችሎታዎችን ንጥረ-ነገሮች ይዞ ይመጣል—ሮሜ 12፡6-8።

3. በሮሜ 12፡6 ስጦታዎቹ በጸጋ መሠረት ይለያያሉ፤ በኤፌሶን 4፡7 ጸጋ የተሰጠው በስጦታ መሠረት ነው፡-

ሀ. ጸጋ ስጦታዎችን የሚያፈራና እንደ አቅርቦት የሚሰጥ መለኮታዊው ሕይወት ነው።

ለ. በሮሜ 12 ስጦታውን የሚያፈራው ጸጋ ነው፤ ስለዚህ ስጦታው በጸጋ መሠረት ነው።

ሐ. በኤፌሶን 4 ጸጋ በስጦታ መሠረት፣ እንደ ስጣታው መጠን ነው።

ሠ. እንደ ሕይወታዊው የክርስቶስ አካል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ “ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ” ከአፋችን ምንም ክፉ ቃል እንዲወጣ መፍቀድ የለብንም—ቁ. 29፡-

1. ለሌሎች የምንናገረው ቃል ጸጋን፣ ክርስቶስን እንደ ድሰታችን እና እንደ አቅርቦታችን የሚያስተላልፍ መሆን አለበት—2 ቆሮ. 13፡14፤ ሮሜ 16፡20፤ 1 ቆሮ. 16፡23፤ ገላ. 6፡18።

2. ሌሎችን የሚገነባው ቃል ለሰሚው ሁልጊዜም ክርስቶስን እንደ ጸጋ ያገለግላል—ኤፌ. 4፡29።

**IV. በኤፌሶን 3፡2 ሐዋርያው ጳውሎስ የተሰጠው የጸጋ መጋቢነት ለአካሉ ብልቶች እንደሆነ ይናገራል—5፡30፡-**

ሀ. በኤፌሶን 3፡2 እና 9 ጳውሎስ *ኦይኮኖሚያ* የሚለውን የግሪክ ቃል ይጠቀማል፤ በቁጥር 9 ይህ ቃል የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ያመለክታል፣ በቁጥር 2 ደግሞ የሐዋሪያውን መጋቢነት ያመለክታል።

ለ. ለክርስቶስ አካል መገንባት እንኖር እና እናገለግል ዘንድ የእግዚአብሔር ጸጋ መጋቢነት ተሰጥቶናል—ቁ. 2-7፡-

1. የጸጋው መጋቢነት ለቤተ ክርስቲያን እንደ የክርስቶስ አካል መፍራት እና መገንባት ወደ ተመረጡት ሕዝቡ የእግዚአብሔር ጸጋ ይታደል ዘንድ ነው—1 ቆሮ. 4፡1-2።

2. ከዚህ መጋቢነት ውስጥ በእግዚአብሔር ቤት መጋቢ የሆነው፣ ለእግዚአብሔር ቤተሰብ ክርስቶስን እንደ የእግዚአብሔር ጸጋ የሚያገለግለው የሐዋርያው አገልግሎት ይመነጫል—9፡17።

3. የጳውሎስ አገልግሎት ለአማኞች  የክርስቶስን ብልጥግናዎች ለድሰታቸው እንደ ጸጋ ማደል ነበር—ኤፌ. 3፡8።

4. የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ በእግዚአብሔር በራሱ ዘንድ ነው፣ የጸጋ መጋቢነት የተሰጠው ግን እንደ አንድ ግለሰብ ለጳውሎስ ብቻ አልነበረም፤ ይህ መጋቢነት ለአማኞች ሁሉ ተሰጥቷል።

5. የጸጋው መጋቢነት አጽናፍ-ዓለማዊ ነው፤ በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መሠረት አማኞች ሁሉ ለክርስቶስ አካል የጸጋ መጋቢነት አላቸው—ቁ. 2፣ 9።

*© 2022 Living Stream Ministry*